# እሳት አቃጠለኝ!




ጠላቴ ሌት ተቀን ሴራ ሲያሴርብኝ፣
በጨለማው ዘመን ብርሃን ከጅሎኝ፣
አጠንክሬ አካሌን ጨምቄ አይምሮዬን፣
በአስታቡልቡል ዘዴ እሳትን ፈጠርኩኝ።

የፈጠርኩት እሳት እኔን እያሞቀኝ፣
ጨለማን ገሽልጦ ሌባውን ሲያሳየኝ፣
ድል ስላበሰለ ለዓመታት ደስ አለኝ።

የድሉን እንጀራ ተምጣድ ሳልስበው፣
እባብ አፍ አውጥቶ ኢሳት ሲሳይ ሲለው፣
እንደ ሄዋን ስቶ ወዲያው አሳረረው።

እንጩት ለቃቅሜ የቀለብኩት እሳት፣
ዕጸ-በለስ ጎርሶ እባብ የጠራው ለት፣
እሳቱ ሲሳይ ነው ይማሰል ያለ ወቅት፣
በነበልባል ምላስ ገረፈኝ በክህደት።

ድሮም እኔ አማረ እጄ አመድ አፋሽ ነው፣
የፈጠርኩት እሳት እያቃጠለኝ ነው!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
የካቲት ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.